האגודה לזכויות האזרח בישראל
جمعية حقوق المواطن في اسرائيل

# መብት
# የኮረናን ትእዛዛት የመጣስ ቅጣቶች



## ጭምብልን መሸፈን

### ጭምብልን መሸፈን በተመለከተ ህጉ ምን ያላል ?

የህዝብ ጤና የሚለው ህግ ሰው ሁሉ በቤቱ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በየትም ቦታ ጭምብሉን የመሸፈን ግዴታ አለው። የዚህ ትእዛዝ ልዩ የሆኑ በህግ የተወሰኑ ኣንድ አንድ ነገሮች አሉ፡ (አንቀጽ 3 (ב) ה ) እና በጤና ጥበቃ ቢሮ በኩል የተወሰኑት ጭምብሉ ያለማድረግ የሚፈቀደላቸው የሚከተሉት ናቸው ፡ ዕድሚያቸው ከ7 ዐመት በታች የሆነ ፤ የኣካል ጉድለት ያላቸው ፤ ስፖርት ሲደረግ ፤ ዝግ በሆነ ቦታ ብቻው የሚገኝ ሰው ፤ (ለምሳሌ እንደ በመኪና ፤ በስራ ቦታ ፤ ተለያይተው በሚሰሩ ሰራተኞች መካከል በ **Opene space** የሚሰራ ከሌላው የ2 ሜትር ርቀት ያላቸው በስራ ቦታ ክፍል ፤ በባህር ዳር ፤ (የ2 ሜትር ርቀት በመጠበቅ)።

መንገድ ላይም ሆነ በጫካ ብቻው የሚገኝ ሰው ጭንብሉን የመሸፈን ግዴታ ያለው ሲሆን ሆኖም ግን በእንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ቅጣት ሳይሆን ማስጠንቀቂያ ብቻ ነው የሚሰጠው፡ ፡

### ጭምብሉ ካልተሸፈኑ ቅጣቱ የመስጠት ስልጣን ያለው ማን ነው ?

ጭምብል ላልተሸፈኑ ሰዎች ቅጣት የመቅጣት ስልጣን ያላቸው ፖሊስ ፤ የማዘጋጃ ቤት የቁጥጥር ስራ ሰራተኞች ፤ ወይም ለዚሁ ሲባል የሰለጠኑ ሌሎች የማዘጋጃ ቤት ሰራተኞች ናቸው። የደን ቦታዎችና የብሄራዊ ፓርኮች ሰራተኞች በቦታው የጭንብል መሸፈኑ ህግ ለተላለፉ ሰዎች ቅጣት የመስጠት ስላጣን አላቸው።

### ጭምብል ያለማድረግ ቅጣት ምን ያህል ነው ?

ቅጣቱ 500 ሸቀል ነው። ተግባሩ በተደጋጋሚ ከሆነ ቅጣቱ ወደ (1000 ሼ) ከፍ ይላል።



## ማንነትን የማወቅ ጥያቄ

### ፖሊስ ወይም ተቆጣጣሪ ማንነቴን ለማወቅ ቢጠይቀኝ የመንገር ግዴታ አለኝን ?

ፖሊስ ከዜጋ ማታወቂያህን ስጥ በማለት የመጠየቁ ጉዳይ እስከ ምን ያህል ነው በሚለው የዜጎች መብት አስከባሪ የሚባለው ድርጂት ከሌሎች ድርጂቶች ጋር በመተባበር ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው የአቤቱታ ጥያቄ በመታየት ላይ ይገኛል። ፖሊስ በተለመደው አሰራር ዝም ብሎ ሳይሆን በቂ ምክንያት ካለው ከዜጋ ማታወቂያ ለማየት መጠየቅ ይችላል። ኮሮናን ለመታገል ሲባል በተደነገጉት ህጎች መሰረት አንድ ዜጋ ህጉን ከጣሰ ፤ ለምሳሌ ብቻውን የመቆየት ግዴታ ካለው ለማወቅ ያህልና ለመቅጣቱ ፖሊስ

ማታወቂያውን የማየቱ ጥያቄ በተመለከተ የመጠየቅ ስልጣኑ ተረጋግጧል። ይህን በተመለከተ ማታወቂያህን ለማየት ፖሊስ ከጠየቀህ የማሳየትነ ግዴታ አለብህ። የኮረናው ትግል በሚል በወጣው ህግ መሰረት ጭምብል ያለ መሸፈን ቅጣት የመዛገጃ ቤት እና የመንግስት ሰራተኞች ቅጣት የመቅጣት ስልጣን አላቸው። ስለሆነ ቅጣቱን ለመስጠት እንዲችል ማታወቂያ መስጠት ግዴታ ነው።

### ማታወቂያ አልሰጥም ካሉ ፖሊስ ምን ማድረግ ይፈቀድለታል (ይችላል)?

የፖሊሱ ጥያቄ ህጋዊ ከሆነ ማንነቴን አልነግርም (ማታወቂያየ አልሰጥም) ካልኩና ፖሊሱ ለማወቅ አንተን ይዞ ፖሊስ ጣቢያ ወስዶ ማጣራት ይቻላል።ማንነቴን አልነግርም ማለት ህጋዊ ትዛዝ አልቀበልም እንደማለት ተቆጥሮ ህግ የመጣስ ወንጀልም ሊሆን ይችላል።

### ማንነቴን አልገልጽም ካልክ የመዛገጃ ቤት ሰራተኛ (የቁጥጥር ስራ ሰራተኛ) ምን ማድረግ ይፈቀድለታል?

(በደን ቦታ ካልሆነ በስተቀር) የመዛገጃ ቤት ተራ ሰራተኛ ማንነቴን አላሳውቅም ያለ ሰው በሐይል የመያዝ ስልጣን የለውም። ቢሆንም ለሰራተኛው ማንነቴን አልገልጽም ማለቱ ህግ እንደመጣስ ሊቆጠር ይችላል።



## በሰላማዊ ሰልፍ መሳተፍና ርቀት አለመጠበቅ

### በሰላማዊ ሰልፍ ተሳትፌ አለሁ። መሳተፌና በብዛት ከሰዎች ጋር በመሰባሰቤ ምክንያት ቅጣት ሊያስቀጣኝ ይችላልን ?

ክልክል በሆነ በሰዎች መሰባሰብ መሳተፍ ቅጣት አያስቀጣም። ቢሆንም መሰባሰቡ እንዲበታተን ፖሊሰስ ካዘዘ የፖሉስ ትእዛዝ አለማክበር የ1.000 ሸቀል ቅጣት ያስቀጣል።

በአጠቃላይ ፤ ክፍት በሆነ ቦታ እስከ 20 ሰዎች ፤ በአደራሺም ሆነ በሌላ መሰባሰቢያ ቦታ እስከ 10 ሰው በአንድ ላይ መገኘት ይቻላል (በድርጂት ቦታዎች(እንደ የቦታው አይነት ይለያል)። በህዝባዊ ክፍት ቦታዎች ለመሰብሰብ የተፈቀደም ቢሆን በሰዎቹ መካከል የ2 ሜትር ርቀት መጠበቅ አለበት። ይህ ትእዛዝ በአንድ ቤት አብሮው የሚኖሩ ሰዎች አይመለከትም።

ሰላማዊ ስልፍ ፡

በሰላማዊ ሰልፍ ስንት ሰዎች መሳተፍ እንዳለባቸው በሚወጡት መመሪያዎች የተወሰነ ነገር ባይኖርም ከሰው ወደ ሰው ቢያንስ የ2 ሜትር ርቀት መጠበቁ ግዴታ ነው። ሰላማዊ ሰልፍ በሚያካሄዱት መካከል ርቀት የመጠበቁ ትእዛዝ ካላከበሩ መሰብሰባቸው እንዲበታተን ፖሊስ ማዘዝ ይችላል። ትእዛዙ ካላከበሩ የ1.000 ሸቀል ቅጣት የሚቀጡ ሲሆን ከደገሙም ቅጣታቸው እጥፍ ይሆናል ። እንዲሁም ርቀት የመጠበቁ ህግ ሲጣስና የተነገራቸው ካላከበሩ ተላላፊዎቹን ፖሊስ ተመጣጣኝ በሆነ ሀይል በመጠቀም

ሊበትናቸው ይችላል።

### የ2 ሜትር ርቀት ኣለመጠበቁ ያስቀጣልን ?

ትእዛዙ የሚለው ከሰው ወደ ሰው የ2 ሜትር ርቀት መጠበቅ ነው። ቢሆንም ርቀቱ አለመጠበቅ አያስቀጣም። ያም ሆነ ይህ ክፍ ብሎ እንደተጠቀሰው (የመሰባሰብ ፤ ሰላማዊ ሰልፍ ወ.ዘ.ተ ) የመሳሰሉት ከህግ ውጭ የሆኑ ተግባራት ከተሰሩ ፖሊስ መሰባሰቡ ለመበተን ከመቻሉም በተጨማሪ ትእዛዙ ካላከበሩ ቅጣት ያስቀጣል።



## የገንዘብ ቅጣት ከተሰጠኝ ምን ማድረግ አለብኝ ?

**ጭንብል አለማድረግ እንደመሰለ ኮሮናው የሚመለከት ህግ ባለማክበሬ ቅጣት ከተሰጠኝ በኋላ ምን አማራጭ አለኝ ?**

ቅጣቱ ከተሰጠህ ዕለት አንስቶ በ60 ቀን ውስጥ መክፈል አለብህ። ቅጣቱ መሰጠቱ ህጋዊ አይደለም የምትሉ ከሆነ እንዲሰረዝላችሁ ወይም በፍ/ቤት እንዲታይላችሁ ከተሰጣችሁ አንስቶ በ30 ቀን ውስጥ ፖሊስ ጣቢያ ታመለክታላችሁ። (ሁለቱ ጥያቂዎች በኣንድ ላይ ማቅርብ ኤቻለም)። ቅጣቱ የመሰረዝ ጥያቄው አይሆንም ከተባለ ከተባለበት ዕለት አንስቶ በ30 ቀን ውስጥ በፍ/ቤት እንዲታይ መጠየቅ ይቻላል። ጥያቄው ሲቀርብ የቅጣቱ የተሰጣችሁ ዋናው ወረቀትና ፤ የጥያቄው ምክንየቶችም በጽሁፍና የማታወቂያ ፎቶ ኮፒ አያይዞ ማቅረብ ይገባል ።

ቅጣቱ እንዲሰረዝ ወይም ፍ/ቤት የመቅረቡ ጥያቄው በጊዜው ማቅረብ የማይቻል ኖሮ ከሆነ ቅጣቱ ወዲያውኑ መከፈል አለበት።

## በጊዜው ካልከፈልኩትስ ምን ይሆናል ?

ቅጣቱ ይሰረዝልኝ የሚለው ጥያቄ ቅጣቱ የሚከፈልበት ጊዜ ስለማይለውጥ በ60 ቀን ውስጥ መከፈል አለበት። ካልሆነ ወደ የእምቢተኞች በግድ የማስከፈል ክፍል ተላልፎ የማስገደዱ ሂደት ይካሄድና በዚህ ሁኔታ ዋናው ከፍያ ወለድ ይጨምራል።ጥያቄው ቅጣቱ ከተሰጠኝ በ30 ቀን ውስጥ ከቀረበ በቅጣቱ ለውጥ አይኖርም( አስከ ፍርዱ ጊዜ ወለድ አይጨምርም)።ቅጣቱ እንዲሰረዝ የሚል ጥያቄ ካቀረባችሁበት ጊዜ በ60 ቀን ውስጥ መልስ ካልተሰጣችሁ ወደ እምቢተኞች ባለ እዳ ክፍል የማስከፈል ሂደት መቅረቡ ለመግታት ያህል ክፈሉት። ቅጣቱ የመሰረዝ ያቀረባችሁት ጥያቄ አይሆንም ከተበለና ለጊዜው ከፍላችሁት ከሆነና ፍ/ቤት የምትቀርቡ ከሆነ የከፈላችሁት ቅጣት ፍ/ቤት እስክትቀርቡ ድረስ ይመለስላችኋል። ቅጣቱ ካልከፈላችሁ ፤ በፍ/ቤት እንዲታይላችሁ አመልክታችሁ ከሆነ የሚከፈልበት የ60 ቀን ጊዜም ካለቀ ጉዳዩ ወደ የእምቢተኞች በግድ ማስከፈያ ክፍል ሂደት አልፎ የ50% ወለድ ይጨመርበታል።

የአስገድዶ ማስከፈሉ ሰራጠኛ (ባለ ስልጣን) ባለ እዳው በተመለከተ ማስረጃ በመጠየቅ የባንኩ ሂሳብና ሌላ ንብረቱ እንዲታገድ ማድረግ ይችላል፡፤

## በፍ/ቤት እንዲታይልኝ ከጠየቅኩ ጉዳዩ በፍ/ቤቱ በእርግጥ ይታያልን ?

ከሳሹ (አቃቤ ህግ) የእራሱ ሀሳባ አለው-ክስ ማቅረብ ወይም አለማቅረብ በሚል። በአጠቃለይ ግን ክስ ይቀርባል እንዳይቀርብ የሚያደርግ ልዩ ምክንያት ካለ በስተቀር። ቅጣቱ በመብዛቱ ምክንያትና በዚህ የተነሳ በፍ/ቤቶች ላይ ጫና ይፈጥራል በሚል አንከፍልም ባዮቹ ፍርድ ማቅረባቸው በተመለከተ ምናልባት ሀገሪቱ አስተያየት ታደርግ ይሆናል የሚል ግምት አለ። ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ይህን በተመለከተ ያለፈ ውሳኔ ስለሌለ በዚህ በመተማመን የሚሰራ ሰው የእራሱ ሃሉፊነት ነው።

**ጉዳዩ በፍ/ቤት እንዲታይልኝ ከጠየቅኩ በኋላ ጠበቃ ያስፈልገኛልን ?**

በፍ/ቤት እንዲታይልህ ከጠየቅክ በኋላና ክስ ከተከሰስክ ከወራት በኋላ የመታየቱ ቀን ፍ/ቤት ቀጠሮ ይይዛል፡ ወደ ፍ/ቤቱ ያለ ጠበቃም መቅረብ ይቻላል፡፡

**ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ሲቀመጥ (ሲያይ) ምን መወስን ይችላል ?**

ቅጣቱ ትክክል አይደለም የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ከሌላችሁ በፍ/ቤቱ እንዲታይላችሁ ከመጠየቅ ብትቆጠቡ ይመረጣል፡፡ ከረታችሁ ቅጣቱ ይመለስላችኋል፡፡ከተረታችሁ ግን ፍ/ቤቱ ከፍ ያለ ተጨማሪ ቅጣት ሊቀጣችሁ እንደሚችል እወቁ፡፡ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ሲያስተላልፍ የተከሳሹ ሁኔታ አይቶ አጥንቶ የቅጣቱ ገንዘብ የመቀነስ የመሳሰሉ አስተያየቶች የሚያደርግበት ሁኔታም አለ፡፡

## ወንጀል



**የኮሮናው ህግ ጥሳሀል በሚል ሰውን ፍ/ቤት ማቅረብ ይቻላልን ?**

ይቻላል፡፡ በገንዘብ ቅጣት ፈንታ ሰውን ይከሰስ አይከሰስ በሚለው አቃቢ ህግ አስተሳሰብ አለው፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ሰውየው የግንዘብ ቅጣት ካልተቀጣ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ወደ ፍ/ቤት የመከሰሱ ጉዳይ መራር የህግ መተላለፍ ወይም እያወቀ በተደጋጋሚ ህጉን ከተላለፈ ነው፡፡መክሰስ በተመለከተ የዜጎች መብት ጥበቃ ድርጂት ባቀረበው ጥያቄ መሰረት የመንግስት የህግ አማካሪ ምክትል ያወጣውን ጽሁፍ አንብቡ፡፡

የዚህ አይነት(የኮረናው) ህግ ያለማክበር እና የወንጀል ክስ የሚያገናኝ አላቸውን ?

በፖሊስ ትእዛዝ መሰረት ጭምብል አለመሸፈንና የሰዎችን መሰባሰብ አለመበተን የፍታሀብሄር ህግን እንደመተላለፍ የሚቆጠር ነው፡፡ ወንጀል ከመፈጸም የሚለየው በወንጀል ከሚኖሮው የክስ ፋይል ሳይሆን የኮሮናው ቅጣቱ ከተከፈለ የክስ ፋይሉ ተዘግቶ ተሰርዞ እንዳልነበረ ይሆናል፡፡

*ይህ የመብት መግለጫ አጣቃላይ ማስራጃ ስለሆነ ህግን በተመለከተ ምክር የሚሰጥ አይደለም፡፡*